# **ጁንታው ሲያቀረሽ፣ ያረግዳል አልባሽ!**

መንግስቴ ደፋር-
(ፍራንክፈርት-ፌብ-2012)

ግራዚያኒ ነፍስ ዘርቶ፣....... ደፍሮ ታሪኩን ከዘከረን፣
ፋሽዝም ጥርስ አውጥቶ፣...... ጥፍር አብቅሎ ከቧጠጠን፣
መንታ ምላሱን መዞ፣..... የቂም ደም ነክሮ፣ ከሰፌፈን፣
እርጉም መንፈሱን፣ ነፍስ ዘርቶ፣...... ቀንድ አብቅሎ ከወጋን፣
አንጋች፣ ሹምባሽ፣ አደራጅርቶ፣..... ባደባባይ ከሞገተን፣
ከእንግዲህማ ምን ቀረልን፣..............
............ዛሬም እንደትላንቱ፣ ተረኞቹ ያው እኛው ነን።

ወገን፣ እንደ ሰባ ፍሪዳ፣...... ለስልጣን ጭዳ ሲታረድ፣
የሰው ገላ ተዘልዝሎ፣..... ብልት እየወጣለት ሲጣድ፣
እግረሙቅና አኮርባጅ፣...... በገላ ላይ ሲረማመድ፣
ያገር ልጅ ተሸልቶ፣...... ጠንብቶ ሲጣል በየመንገድ፣
በዱር በገደል በከተማው፣....... ስንቱ ሲገባ ካውሬ ሆድ፣
ምን ያልሆነው ቀርቶ ይሆን?...... ፀብ ያለሽ፣ በደቦ ያሉን የግድ።

ትንሽ ትልቁ ሲማገድ፣..... ብስል ከቀሊል ሳይለይ፣
እናትና አባት እንኳ ሳይቀር፣..... በወለደ ፍዳውን ሲያይ፣
ምድሪቱ ምጣድ ሆና፣...... በጥይት አረር ስትጋይ፣
ጁንታ በእብሪት ልቡ፣...... ከዳር እስከዳር ሲናኝ፣
ጀሌው እንደቀትር እባብ፣...... እየተዎረወረ፣ ነፍስ ሲያበራይ
ወገን መሸሸጊያ አጥቶ፣............
..................በዱር ቀርቷል፣  ላሞራና ላውሬ ሲሳይ።

የባብ እንቁላል ስሪት፣...... የጥንብ አንሳ፣ የሳቢሳ፣
የበረሃ ገመሎ፣...... በቁሙ ነፍሰ በላ፣ የሰው አሳ፣
የውስጥ ቁስል የአንጀት እዥ፣..... የሚያመረቅዝ ነቀርሳ፣
ሳይፈልጉት የበቀለ፣...... ተጠምጣሚ እንደ ስሚዣ፣
ነጣቂ አውሬ የጅብ መንጋ፣..... ለወገኑ እማይሳሳ፣
ነፍስ በላ እርድ ምሱ፣...... የለከፈው ባርባ ባምሳ።

የታሪክ ማቅ፣ የበደል ድር፣.....የሸመነ የእብሪት ደውር፣
ግብረ-ዝቃጭ፣ የእብሪት ጥንስስ፣...... ያመፅ ጓዳ፣ ዝክረ ሽብር፣
የታሪክ ድር አራሙቻ፣.....  አክብሩኝ  ባይ፣ የሾህ አጥር፣
እርኩስ ገመናን ከፈን ሊያለብስ፣...... ሙሾ በሾርኒ ሲደረድር፣
በሀገር በደል ማፈር ቀርቶ፣...... ጀብዱ ሆኖ  ሲፎክር።
ይህ ነው ግማደ-ታሪኩ ሲታይ!...... ትንሳኤ ደርግ ሲዘከር፣

ጁንታው ባናቱ ሲቀረሽ፣...... በእፍኙ ቃል ተቀባይ፣
አንጋች፣ አልባሽ፣ መሰሪ፣...... እመሸበት አዳሪ፣ ንገሩኝ ባይ፣
የሰው ያውሬ ቅልቅል፣..... የቀንድ-አውጣ ዘር፣ ውስጠ ሰላይ፣
ተሹለክላኪ በደም ሥር፣....... በራዥ፣ ንፁህ አካል በካይ፣
ያባቱ ልጅ ቂመኛ፣...... የበረሃ እባብ፣ የጊንጥ መርዝ ሾተል ንቃይ፣
ያገር፣ የሰው ምች መጋኛ፣....... ከሰው ካውሬ  እማይለይ፣
ትላንት፣ የገንጣይ አስገንጣይ ደብተራ፣..... ዛሬ፣ የፋሽዝም ማድ አገልጋይ፣

ተኝተን ቢያየን ከመስኩ ላይ፣...... ፈተሸኝን አሉ በሰላይ፣
ሰኔና ሰኞ ገጥሞ፣...... ሰርግና ምላሻችን፣ እስኪቦካ ባንድ ላይ፣
እንዳኛለን በጉራህ ጠናኝ፣..... እንግዲህ አኩል ከሆንማ አውሮፓ ላይ፣
ትላንትም እኛው ተገዳይ፣..... ዛሬም እኛው ተበዳይ።

**እግዚአብሐር አትዮጵያን ይባርክ!**